**የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቤተ መፃህፍት**
**የተቆጣጣሪ አልባ ህፃናት መመሪያ**
**መስከረም 9 ቀን 2013 ዓ.ም. የተሻሻለ**

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቤተ መፃህፍት ልጆች ቤተ መፃህፍት እንዲጎበኙ፣ ፕሮግራሞችን እንዲከታተሉና የቤተ መፃህፍት ስብስቦችንና ኮምፒዩተሮችን እንዲጠቀሙ የሚያስችል ምቹ የሆነ አካባቢን ለመፍጠር ተግቶ ይሠራል። የቤተ መፃህፍት ሠራተኞች ህፃናት ቤተ መፃህፍት በሚጠቀሙበት ጊዜ ህፃናቱን ለመተባባርና ለማገዝ ዝግጁ ነው። የልጆች የቤተ መፃህፍት ቦታ ለልጆች፣ ለወላጆቻቸው፣ ለአሳዳጊዎቻቸው፣ ለአስተማሪዎቻቸውና ለተንከባካቢዎቻቸው እንዲሁም የለጆች መፃህፍትንና ሌሎች የቤተ መፃህፍት ቁሳቁሶችን ለሚጠቀሙ ሰዎች ብቻ የተፈቀደ ነው።

ቤተ መፃህፍቱ ልጆችና ወላጆቻቸው አዘውትረው ወደ ቤተ መፃህፍት እንዲመጡ ያበረታታል። ይሁን እንጅ የቤተ መፃህፍት ሠራተኞች ለልጆች እንክብካቤ ሊሰጡ አይችሉም ወይም የልጆቹን ደህንነት በተመለከተ ኃላፊነት አይወስዱም። ቤተ መፃህፍት ለሚጎበኙ ልጆች ባህሪና ደህንነት ኃላፊነት መውሰድ ያለባቸው የቤተ መፃህፍት ሠራተኞች ሳይሆኑ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ አስተማሪዎችና ተንከባካቢዎች ናቸው። ተቆጣጣሪ የሌላቸውን ልጆች የቤተ መፃህፍት ሠራተኞች እንዲቆጣጠሩ መደረግ የለባቸውም።

**በቤተ መፃህፍቱ ተቆጣጣሪ አልባ ልጆችን የሚመለከቱ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ይከናወናሉ፡**

- እንደሁሉም የቤተ መፃህፍት ተጠቃሚዎች ሁሉ ልጆች የቤተ መፃህፍት ንብረትን ማክበር እንዲሁም የቤተ መፃህፍቱ አሠርና ሂደት በሚፈቅድ መልኩ መስተናገድ ይኖርባቸዋል። ልጆች ለቤተ መፃህፍቱ የሥነ ምግባር ደንቦች ተገዥ መሆን ይጠበቅባቸዋል።
- ስምንት (8) ዓመትና ከዛ በታች የሆኑ ልጆች በማንኛውም ሰዓት ቢሆን በወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ክትትል ሊያደርጉላቸው ይገባል ወይም አስራ ሶስት (13) ወይም ከዛ በላይ ዕድሜ ያለው ሰው እንደተቆጣጣሪ ሊመደብላቸው ይገባል። ዕድሜያቸው ስምንት (8) ዓመትና ከዛ በታች የሆኑ ልጆች ብቻቸውን ከሆኑ ሠራተኞች ወላጆቻቸውን/አሳዳጊዎቻቸውን ለማነጋገር ይሞክራሉ። ወላጆቻቸውን/አሳዳጊዎቻቸውን ማግኘት ካለተቻለ የሚመለከታቸውን ባለሥልጣናት ያነጋግራሉ።
- የቤተ መፃህፍት ደንቦችና ሥነ ምግባርን መከተል እስከቻሉ ድረስ ዕድሚያቸው ዘጠኝ (9) እና ከዛ በላይ የሆናቸው ልጆች ቤተ መፃህፍቱን ያለተቆጣጣሪ መጠቀም ይችላሉ።
- በማንኛውም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ውሳኔን ሊያዛባ የሚችል የአዕምሮ፣ የአካል ወይም የስነ ልቦና በሽታ ያለባቸው ወይም የቅርብ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ልጆች ምን ጊዜም ቢሆን በወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ወይም እንዲከታተላቸው በተመደበላቸው ሰው አማካኝነት ቁጥጥር ስር መሆን አለባቸው።
- አስር (10) ዓመት ወይም ከዛ በታች የሆነው ልጅ ቤተ መፃህፍቱ በሚዘጋበት ሰዓት ያለምንም ማጓጓዣ ቤተ መፃህፍት ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲቀር ከተደረገ ጉዳዩ ወደ ፖሊስ ይመራል። በምንም ዓይነት ሁኔታ የቤተ መፃህፍት ሠራተኛ ልጆቹን ከቤተ መፃህፍቱ ህንፃ ውጭ አያጓግዝም ወይም አያንቀሳቅስም።
- ከቤተ መፃህፍቱ ህንፃ ወይም በቤተ መፃህፍቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በመጫወት ወይም የትራንስፖርት አገልግሎት በመጠባበቅ ላይ ለሚገኙ ልጆች ቤተ መፃህፍቱ ኃላፊነት አይወስድም።
- በዲሲ የኦፊሴል ኮድ §32-221 መሠረት “ማንኛውም የንግድ ሥራ ባለቤት ወይም ሠራተኛ ከ16 ዓመት በታች የሆነ ልጅ ያለፈቃድ ከትምህርት ቤት እንደቀረ ካመኑ በትምህርት ክፍለ ጊዚያት በንግድ ይዞታው ሥራ ፈትቶ እንዲቆይ ማድረግ አይችልም።”